SUBURBAN MARYLAND

# WELCOME BACK CENTER

FOR FOREIGN-TRAINED HEALTH PROFESSIONALS

## ምን፥

የዌል ካም ባክ ሴንተር ኦፍ ስበርባን  ሜሪላንድ በአይነቱ  ልዩ የሆነ ማዕከል ነው:: ማዕከሉ በተለያዩ አገሮች በጤና መስክ የሰለጠኑ እንዲሁም የስራ ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎቻ የትምህርት እና የስራ ልምዳቸዉን ተጠቅመዉ የተሻለ የስራ ዕድል እንዲያግኙ ፥በዘርፉ ያለዉን የጤና ባለሙያዎቻ  እጥረት ለማቃለል ይሰራል:: ይህም ከተለያየ ቋንቋ እና ባህል የተውጣጡ የጤና ባለሙያዎችን ቁጥር በማሳደግ በሜሪላንድ ያለዉን የጤና አገልግሎት ለሁሉም ለማዳረስ የሚደረገዉን ጥረት ያግዛል::

## ምን፥

በ 2006 የላቲኖ ሄልዝ ኢንሸቲቭ በሞንትጎሞሪ ካዉንቲ ሄልዝ ኤንድ ሂዩማን ሰርቪስ በዉጪ የሰለጠኑ የጤና ባለሙያዎች በሜሪላንድ የሙያ ማረጋገጫ ሰርትፊኬት እንዲያገኙ ለማገዝ ተቋቋመ፥፥ በ 2010 ፕሮግራሙ ስያሜዉን ወደ ዌል ካም ባክ ሴንተር ኦፍ ስበርባን ሜሪላንድ በማለት የዌል ካም ባክ ኢኒሸቲቭ አካል ሆኗል፥፥

## የት፥

በሜሪላንድ ሞንትጎሞሪ ፣ፕሪንስ ጆርጅስና ፍሬድሪክ ካዉንቲ የሚኖሩ በዉጪ አገር ለሰለጠኑ የጤና ባለሙያዎች አገልግሎት ይሰጣል፥፥

## ለምን፥

በተለያዩ አገሮች በጤና መስክ በቂ የትምህርት ና የሰራ ልምድ ያላቸው በሜሪላንድ የሚኖሩ ስደተኞች ያላቸዉን የትምህርት እና የስራ ልምድ ወደ ጎን በመተዉ በአነስተኛ ሥራ ላይ ተሰማርተዉ ማበርከት የሚችሉትን አስተዎጽኦ ሳያደርጉ ቆይተዋል፥ ስለሆነም ማዕከሉ የሚሠጠዉ  አገልግሎት በጤና ዘርፍ ውስጥ ያለዉን  የባለሙያዎች ስብጥር ከማስፋት ባሻገር በህመምተኞች ና በጤና ባለሙያዎች መካከል የተሻለ መግባባት በመፍጠር ሁሉም ኗሪ አስተማማኝ የጤና አገልግሎት እንዲገኙ  ትልቅ እገዛ ያደርጋል፥፥

## እንዴት፥

ማእከሉ ግቦቹን ለማሳካት ፤

- ለሁሉም ተሳታፊዎች የአንድ ለአንድ ምክር እና ድጋፍ ፣
- ትምህርታዊ ስልጠና፣ የእንግሊዘኛ ቋንቋ እና የቦርድ ፈተና ዝግጅት
- በሜሪላንድ ሆስፒታሎች እና በሌሎች የጤና ማዕከላት ስለ አሜሪካ የጤና አገልግሎት በተግባር የስራ ልምድና ተሞክሮዎችን እንዲያገኙ ማገዝ
- በሰለጠኑበት ሙያ ሥራ እንዲያገኙ የቅድመ ቅጥር፥የሥራ ተነሳሽነት ና ብቁነት ስልጠና መስጠት
- ባህልን ያገናዘበ የአመራር ችሎታ እንዲኖራቸዉ ማገዝ

## እነማን፥

የማእከሉ አጋሮች የአካባቢ ና የስቴት መንግስታት፣ የትምህርት ማእከሎች እንዲሁም  የጤና ባለሙያ  ቀጣሪ ድርጅቶች ናቸዉ። እንዴት መሳተፍ እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጉ በስልክ ቁጥር 240-777-3168.፤ ወይንም የሚከተለዉን ድህረ ገጽ http://lhiinfo.org/en/programs-and-activities/welcome-back-center-of-suburban-maryland/  ማግኘት ይችላሉ::

MONTGOMERY COUNTY MARYLAND

June 2015